ספריית פיג'מה

## המשך פעילויות בעקבות הסיפור - የኔቮ ጭምብል



በ: ሐቫ ዲቦን
ምሳሌዎች: ኢታይ ቤኪን
הוֹצָאָה: כנרת
የእድሜ ክልል: መዋዕለ ሕጻናት

שִׂיחָה

**ለቤተሰባዊ ንባብ የሚበጅ ምክር**

አንድ መጽሐፍ ለአንድ ልዩ ዝግጅት ለመዘጋጀት ወይም ካለፈ ክስተት ላይ ትውስታዎችን ለመሰብሰብ ይረዳል። የበዓል ሰሞን ለምሳሌ ከበዓል ጋር የተያያዘ መጽሐፍ መምረጥና መወያየት ይችላሉ፡- በበዓል ቀን ምን ምን ዝግጅቶች ለእርስዎ ታቅደዋል? ሲቃረብስ ወላጆችና ልጆች አብረው እንዴት ማዘጋጀት ይችላሉ? ለፑሪም ዝግጅት አንድ ላይ ልብስን መላበስ ወይም ምግቦችን መላክ ይችላሉ። ከበዓል በኋላም መጽሐፉን እንደገና ማንበብና በእርሱ በመታገዝ አብረው ያጋጠሟችሁን መልካም ጊዜያት ያስታውሱ።

מִשְׂחָק

**የመላበሶች ጨዋታ**

በቤቱ ዙሪያ በመዞር የሆነን ነገር ምረጡ፡- ማንኪያ፣ የአበባ ማስቀመጫ፣ ኳስ ወይም ... ምንጣፍ። እያንዳንዱ የተመረጠውን ዕቃ የሚያካትት መላበስ ይገልፃል፡- ምንጣፍ የምንጣፍ ሻጭ ሴት ልብስ አካል ሊሆን ይችላል? ወይስ ምናልባት እርሱ የሚበር ምንጣፍ ሊሆን ይችላል? ኳሱ የአንድ ስፖርተኛ ልብስ አካል ሊሆን ይችላል? ወይስ ?ምናልባት የቀልደኛ አፍንጫ

כְּלָלִי

**መላበሶች በምስሎች**

በመጽሐፉ ውስጥ የጠፈር ተመራማሪ አለባበስ የት ላይ ነው ያለው? ንግስት አስቴርን፣ የእሳት አደጋ ተዋጊዎችን፣“ ፖሊሶችን ወይም አልበርት አንስታይንን በተመለከተስ? በምስሎቹ ውስጥ ልብሶችን መፈለግ ትችላላችሁ። በተለይ ?የትኛውን መላበስ ይወዳሉ

**?አልበርት አንስታይን ማን ነበር**

አልበርት አንስታይን [1879-1955] የጀርመን ተወላጅ አይሁዳዊ ሳይንቲስት ነበር። እርሱ ባዘጋጀው “”የአንፃራዊነት ፅንሰ-ሀሳብ”” ባደረጋቸው ሌሎች ጥናቶች በመታገዝ በሳይንሱ ዓለምና በተፈጥሮ፣ በጊዜ ብሎም በዩኒቨርስ ህጎች ግንዛቤ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል። አንስታይን በቀልድና ምናብ ተሰጥኦ የተካነ ነበር። ለሰላምና ለወንድማማችነት የሰራ ሲሆን ከመላው ዓለም ካሉ ልጆች ጋር መጻጻፍ ይወድ ነበር። አንስታይን በኢየሩሳሌምና በእስራኤል ግዛት ስር ”የዕብራይስጥ ዩኒቨርስቲ እንዲቋቋም ድጋፍ አድርጓል።

הַעֲשָׁרָה

**ፒንተረስት**

[ተጨማሪ ስራዎችን፣ መዝሙሮችንና እንቅስቃሴዎችን በፒጃማ ቤተ መጻሕፍት ፒንተረስት ላይ]

הַשְׁרָאָה

**መላበሶችና ፑሪም**

**መጽሐፉ የፑሪም በዓል ትውስታዎችን ለማካፈል እድል ይፈጥራል፡- መላበስ ትፈልጋላችሁ? የምትላበሱትስ በፑሪም ብቻ ነው? እናንተ ወላጆች በልጅነታችሁ ጊዜ ልብስ መላበስ ትወዱ ነበር? የትኛውን መላበስ በደንብ ታስታውሳላችሁ? – ማን መልበስ እንደሚወድና ማን እንደማይወድ መስማትና ያለፉትን ፎቶዎች በመመልከት የፑሪም ልዩ ጊዜዎችን ማስታወስ ትችላላችሁ።**

סִרְטוֹנִים

እያንዳንዳችን በሆነ ነገር እንለያለን። የQR ኮዱን ስካን በማድረግ ኦፐኒክና ከጓደኞቹ "ልዩ" ስለሚለው ቃል የሚነጋገሩትን ታገኛላችሁ።

እያንዳንዳችን በሆነ ነገር እንለያለን። የQR ኮዱን ስካን በማድረግ ኦፐኒክና ከጓደኞቹ “ልዩ” ስለሚለው ቃል የሚነጋገሩትን ታገኛላችሁ።